# ለኅብረተሰቡና ለአገሪቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አዲስ ገቢዎች የሚሰጥ የዓልያና ቅሊጣ ሚኒስትር ሽልማት

ለኅብረተሰቡና ለአገሪቱ ከፍተኛ አስተዋጽ ላበረከቱ አዲስ ገቢዎች የዓልያና ቅሊጣ ሚኒስትሯ የዕውቅና ሽልማት ይሰጣሉ። ሽልማቶቹ አዲስ ገቢዎች ለፈጸሙት የላቀ ተግባር የእስራኤል ኅብረተሰብ ዕውቅናና አድናቆቱን ለመግለጽ በማለት የሚሰጥ ነው። ሽልማቶቹ የሚሰጡት በተለያዩ መስኮች ሲሆን ይህም ሕክምና፣ ሳይንስ፣ ኅብረተሰብ፣ ሥነ ጥበብ፣ ስፖርት፣ ወዘተ. ያጠቃልላል።

ለአሸናፊዎቹ ሽልማቶቹ የሚበረከቱት ክብርት ወ/ሮ ፕኒና ታምኖ-እሽቴ የዓልያና ቅሊጣ ሚኒስትር በሚገኙበት ሥነ ሥርዓት ላይ ሲሆን ዕለቱም ሔሽቫን 7 ቀን 5781 ዓ.ዓ. ወይም እሑድ 25.10.2020 ዓ.ም. በሚውለው የአዲስ ገቢዎች ቀን ላይ ነው።

ለሽልማቱ ዕጩ መሆን የሚቻለው ከ1.1.1984 ዓ.ም. ጀምሮ የአዲስ ገቢ ባለመብትነት ለነበረው ብቻ ነው። በተጨማሪም ዕድሜው ከ21 ዓመት በላይ የሆነና የእስራኤል ዜጋ ሆኖ በአገሪቱ ውስጥ በቋሚነት ለሚኖር ሲሆን ለዕጩነት ከመቅረቡ በፊት ለ5 ዓመት በተከታታይነት እስራኤል ውስጥ የኖረ መሆን አለበት።

የዕውቅና ሽልማቱን መመሪያዎች፣ የዕጩነት ማቅረቢያ ቅጾችን እና ተያይዘው የሚቀርቡ የአባሪ ሰነዶችን ዝርዝሮች [www.mai.gov.il](http://www.mai.gov.il) ከተሰኘው ከዓልያና ቅሊጣ ሚኒስትር ድረ ገጽ ላይ ማየት ይቻላል።

የዕጩዎችን ስም እስከ 26.08.2020 ድረስ ማቅረብ ይቻላል። ስማቸው ከዚህ ቀን በኋላ የሚቀርቡ ግለሰቦች በዕጩዎች ዝርዝር ውስጥ አይካተቱም።

ለተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎች ለኮሚቴው ሰብሳቢ ለኢሬና ሬኡቬኒ በስልክ ቁጥር 073-3972104 ወይም 073-3972113 መደወል ይቻላል።

*በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በተባእታይ ጾታ የተጻፈው ለአንስታይ ጾታም ያገለግላል።